# እየሠሩ የመታደስ እና እየታደሱ የመሥራት መርሕ

ስሚነህ 03-15-17

አገራችን ላለፉት አሥራ አምስት ዓመታት በሁሉም የሥራ መስኮች ከፍተኛ ለውጥ አምጥታለች፡፡ በአገራችን ታሪክ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ እየተካሄደ እና ሂደቱም በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ አመላካች የሆኑ በርከት ያሉ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ እና እየተገነባ በሚገኘው ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የዜጎች እና የልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች የፖለቲካ መብቶች ሕጋዊ ዕውቅና እና ዋስትና ማግኘታቸው አንዱ ማሳያ ሲሆን፤ ሥርዓቱ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን ማንነት ያስከበረ አዲስ ዓይነት ፌዴራላዊ ሥርዓት ነው፡፡ በመሆኑም የሕዝቦች እኩልነት ያስከበረ ሥርዓት ነው። የሃይማኖቶች እኩልነትን ያከበረ ሥርዓት በመፈጠሩም መንግሥት እና ሃይማኖት ተነጣጥለዋል፡፡ የዜጎቻችን እና የመላው ሕዝብ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ቅድሚያ በመስጠት ሥራ ላይ የዋለው ፌዴራላዊ ሥርዓት መሠረት የተጀመረው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሕዝብ የሚጠቀምበት ከመሆኑም ባሻገር በማኅበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በመገንባት ረገድም ረጅም ርቀት ተጉዘናል፡፡

ያም ሆኖ ግን ልማታዊ  የመንግሥትን ሥልጣን የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻል እና አገራዊ ለውጡን ለማስቀጠል ከመጠቀም ይልቅ የግል ኑሮ መሠረት አድርጎ የመመልከት፤ በአንዳንዶችም ዘንድ የግል ጥቅም ከማስቀደም ጋር እየተያያዘ መምጣቱ ሥርዓቱን በብዙ ሁኔታዎች ሲፈታተነው ይታያል። በመሆኑም በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት መዋቅሮች እና ሕዝቡ ድረስ የዘለቀ ጥልቅ ተሃድሶ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ወደ ሥራ ከተገባ ወራት ተቆጥረዋል። ይህ ጽሑፍም የተሃድሶውን ሂደት እና ውጤት የሚቃኝ ሲሆን፤ ለዚህም ከአጀንዳችን ጋር የተያያዘውን እና ገዥው ፓርቲ በተሃድሶው ዋዜማ ላይ ያሰመረበትን ነጥብ ይዳስሳል።

*አገራዊ ለውጡ በስኬት ሲጓዝ የቆየው መንግሥታዊ ሥልጣንን ለሕዝብ ጥቅም ማስከበሪያ ማድረግ በመቻሉ የሆነውን ያህል፤ ይህ ሥልጣንን ያለአግባብ ለመጠቀም ለሚሹ ግለሰቦች*

በመሣሪያነት ማገልገል ሲጀምር የተጀመረው ልማት ይደነቃቀፋል፡፡ መልካም አስተዳደርም ይጠፋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሕዝብን በማስመረር ላይ ያለው ችግር ዋነኛ መንስዔ ይህ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ደረጃው እና መጠኑ ምንም ይሁን ምን የመንግሥት ሥልጣንን ያለአግባብ ለግል ኑሮ መሠረት ለማድረግ የሚታየው ዝንባሌ እና ስህተት መታረም እና መገታት እንዳለበት፤ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ተጨማሪ ርምጃም መውሰድ እንደሚገባ ገኸቸው ፓርቲ ወስኗል፡፡ ዝንባሌው በሚታይባቸው ቦታዎች ሁሉ በአግባቡ እየተፈተሸ እንዲስተካከል እና የድርጅታችን ጥራት እና ጥንካሬ ተጠብቆ እንዲቀጥል አስፈላጊ የሆነው ርምጃ ሁሉ እንዲወሰድም ወስኗል፡፡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በዚህ ረገድ ከራሱ ጀምሮ የሚታዩ የጥገኝነት አስተሳሰቦች እና መገለጫ የሆኑትን ጠባብነት እና ትምክህተኝነትን፤ እንዲሁም የጥገኝነት ተግባራትን በጥብቅ በመታገል ይህ አዝማሚያ እንዲገታ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር ዕቅዶችንም አዘጋጅቷል፡፡

ኢህአዴግ ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ከገጠሙት ከባድ ፈተናዎች ሁሉ ዋነኛ የሆነው መንግሥታዊ ሥልጣን በእጁ ከመግባቱ ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ አምኖ መቀበሉ በራሱ ፈተናውን ለማለፍ የሚያስችል ስንቅ መሰነቁን የሚያመላክት ነው። የመንግሥት ሥልጣንን መያዝ በአቋራጭ ለመክበር እጅግ የተመቸ ሆኖ መገኘቱን በግምገማው አንጥሮ ያወጣው ኢህአዴግ በየደረጃው በወሰደው እርምጃ ውጤታማ መሆኑን በየደረጃው የተደረጉት የጥልቅ ተሃድሶ ውጤቶች እያረጋገጡ ነው። መንግሥታዊ ሥልጣንን ብዙኀኑን የበይ ተመልካችነት ማረጋገጫ አድርጎ ለመጠቀም የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ የድህነትን አዙሪት በማባባስ አገሮችን ወደ ቀውስ እንደሚያመራ የተሟላ ግንዛቤ ያዳበረ ድርጅት መሆኑ፤ በዚህ ግንዛቤ ላይ በመመሥረትም የመንግሥት ሥልጣን ሀብት የመቀራመቻ ሳይሆን፤ የብዙኀኑን ሀብት የመፍጠር እና የመጠቀም ብቃት የመገንቢያ መሣሪያ እንዲሆን ለማድረግ የሰየማቸው መድረኮች ከሞላ ጎደል ውጤታማ መሆናቸው በብዙ አግባቦች ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን፣ ይህ በራሱ አንድ ትልቅ ስኬት ሆኖ አለቀ ደቀቀ ብሎ መዘናጋት ሳይሆን፤ እየታደሱ የመራትን፣ እየሠሩ የመታደስ መርሕን መከተል ይገባል።

እንደሚታወቀው መንግሥት የተፈጠረን ሀብት ከማከፋፈል ይልቅ፣ ሁሌም ቢሆን ብዙኀኑ አዲስ ሀብት እየፈጠረ በብልፅግና ጎዳና እንዲረማመድ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት

አድርጓል፡፡ መንግሥት መላ ትኩረቱን በኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ልማት ላይ አድርጎ በመሥራት ላይ ይገኛል። በዚህ አሠራሩም ቀስስተኛ ሳይሆን፤ ፈጣን እና በየደረጃው ሕዝብ የሚጠቀምበት ዕድገት መገኘቱን አረጋግጧል፤ እያንዳንዱ የመንግሥት በጀት የሕዝብን ሰፊ ጉልበት ለማንቀሳቀስ እርሾ ሆና በትክክለኛ ቦታዋ ላይ እንድትውልም አድርጓል። በእርግጥ ይህ ሂደት እንከን አልባ አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ በየደረጃው ጥቂት የማይባሉ የሥራ አመራሮች ሕዝባዊ እና አገራዊ ኃላፊነታቸውን በመዘንጋት በያዙት ሥልጣን የራሳቸውን ጥቅም ሲያስቀድሙ ታይተዋል።

የ15 ዓመታቱን ጉዞ በጥልቀት የፈተሸት የግምገማ መድረኮች፤ ድርጅቱ ላለፉት 25ም ሆነ ከዚያ በፊት በነበሩት ዓመታት ሕዝባዊ ትግሉን እየመራ ለላቀ ውጤት የበቃ እና አገራችንን በትክክለኛ አቅጣጫ መርቶ ለከፍተኛ ውጤት የበቃ እንደሆነ አረጋግጠዋል። ድርጅቱ ትንንሽ ስህተቶችም ቢሆኑ ከተደጋገሙ ጉዳታቸው ተበራክቶ ከባድ ዋጋ ያስከፍላሉ ብሎ በፅኑ የሚያምን መሆኑ በራሱ እየሠሩ በመታደስ፤ እየታደሱ በመሥራት ሂደት ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን ውጤት ከወዲሁ ለመገመት ያስችላል።

የጥልቅ ተሃድሶው ዋነኛ ዓላማም ከእያንዳንዱ ሂደት ተገቢውን ትምህርት በመውሰድ ስህተቶችን እንዳይደገሙ ለመከላከል ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የተፈፀሙ ስህተቶችን በፍጥነት የማረም እና ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስም ሌላኛው የፓርቲው እምነት ነው። የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነትን እንዲያገኝ ከተፈቀደለት ከምንም ነገር በላይ የሚያዳክመው ራስን በራስ የማረም ችሎታ እና ብቃትን ስለመሆኑ አስቀድሞ የተገነዘበ መንግሥት እና ድርጅት እየሠራ ለመታደስም ሆነ እየታደሰ ለምሥራት የሚከለክለው ኃይል የለምና አካሄዱ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡

ጀማሪ በሆነው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኅብረተሰብ ደረጃ የሕግ የበላይነትን የሚሸረሽሩ ኋላቀር አመላካከቶች እና ፍላጎትን በኃይል የማስፈጸም ዝንባሌ ሊፈታ የሚችለው በአንድ አዳር እና ለስድስት ወር በተደረገ የጥልቅ ተሃድሶ ንቅናቄ ሳይሆን እየሠሩ በመታደስ እና እየታደሱ በመሥራት መርሕ መሆኑን ሕዝቡ ሊገነዘብ እና የሂደቱ አካል ሊሆን ይገባዋል። ተቃውሞዎችን እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ለሕገ ወጥነት ተግባራቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉ ቡድኖች እና ግለሰቦች የጥፋት ሴራቸው ግቡን የሚመታው የመታደስ ውጤቶችን በአንድ አዳር እና ወራት ጠብቆ ተስፋ የሚቆርጥ ማኅበረሰብ ሲንሰራፋ ብቻ

መሆኑንም እየሠሩ መታደስ እና እየታደሱ መሥራት መርሐችን አጥብቀን ልናጤነው ይገባል።

ማንም ሰው በሠላም የመኖር፣ የመሥራት፣ የመማር፣ የመንቀሳቀስ፣ ሀብት የማፍራት፣ የመሰለውን አመለካከት የማራመድ እና የመሳሰሉት መብቶች የሚከበሩለት የሕግ የበላይነትሲኖር ብቻ መሆኑን እስከተገነዘበ ድረስ፣ ይህ የሚታለፈው እየሠሩ በመታደስ እና እየታደሱ በመሥራት መሆኑንም ያለአንዳች ማመንታት ሊቀበል ይገባል፡፡ የሕግ የበላይነት አደጋ ላይ ለመውደቁ የመጀመሪያ ምክንያት ሊሆን የሚችለው፣ በተለያዩ አካባቢዎች የመኖረው ሕዝብ ጥያቄ አለኝ ብሎ ምላሽ ሲፈልግ፣ መንግሥት በአግባቡ ተገቢውን መልስ የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን ሲዘነጋ ነው፡፡ ለጥያቄዎቹ ተገቢውን ምላሽ በአግባቡ እና በጊዜው መስጠት ካልተቻለ የሕዝብ ጥያቄዎችን በመንተራስ ለጥፋት እና ለውድመት የሚነሱ ኃይሎች ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠርላቸዋል፡፡ ስለሆነም እየሠሩ መልስ መስጠት፣ መልስ እየሰጡ መሥራትንም በየደረጃው የሚገኝ የመንግሥት አስፈጻሚ እና ፈጻሚ ጠንቅቆ ሊገነዘበው የሚገባ መሆኑን ሳያሰምሩበት ማለፍ አይገባም፡፡

በጥልቅ ተሃድሶው መድረኮች ዋዜማ በተለያዩ ሥፍራዎች በግለሰቦች እና በመንግሥት ተቋማት ላይ የተፈጸሙት የማውደም ተግባራት በዝርፊያ የታጀቡ በመሆናቸው የሕዝብ ጥያቄ ላልተፈለገ ዓላማ ስለመዋሉ እና ለሥጋት የሚዳርግ ሥርዓት አልበኝነት ስለመንሰራፋቱ ማሳያዎች ናቸው፣ ከእንደዚህ ዓይነት ድንገቴዎች መዳን የሚቻለው ደግሞ ሁሌም የመታደስ እና እየታደሱ የመሥራት መርሕን መከተል ሲቻል ብቻ ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ አካሄድ ጥያቄ አለኝ ብሎ ለተነሳ ሕጋዊ እና ሠላማዊ ሕዝብ፣ መንግሥትን በአግባቡ እና በፍጥነት ምላሽ ለመስጠት ያስችለዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ሥራ ፈቶ መታደስም ሆነ ሥራ ላይ ቁጭ ብሎ በተሃድሶ ሂደት ውስጥ አለማለፍ የሕዝብ ጥያቄ እንዲደራረብ እና የምላሽ አሰጣጥ ሥርዓቱ ዘገምተኛ እንዲሆን በር ይከፍታል። አገርን እና ሕዝብን ትርምስ ውስጥ የሚከቱ ሁኔታዎች የሚፈጠሩት ከዚህ መርሕ ባፈነገጠ አሠራር ውስጥ ስንዘፈቅ ነው። አደገኛ ድርጊቶች እንዲወገዱ፣ የሕዝብ ሠላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በሕገ ወጦች እንዳይጠለፉ እና የሕግ የበላይነት ልዕልና እንዲያገኝ ካስፈለገ እየሠሩ መታደስን እና እየታደሱ መሥራትን ሙጥኝ ማለት ያስፈልጋል።

እየታደሱ የመሥራት እየሠሩ የመታደስ መርሕ የሕግ የበላይነት፣ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተግባር እንዲረጋገጡ፣ ፍትሐዊ የሀብት እና የሥልጣን ክፍፍል እንዲሰፍን፣ ዜጎች በመንግሥት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ቀረፃ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውክል እና እንዲኖራቸው፣ በሥልጣን ያላግባብ መገልገል እንዳይኖር፣ በሙስና መበልፀግ ነውር እንዲሆን፣ በአገር ጉዳይ ዜጎች የባለቤትነት ስሜታቸው እንዲጎለብት፣ ወዘተ. የሚረዳ ፍቱን መሣሪያ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው መንገድ እንደዚህ ዓይነቱን የሠለጠነ እና ዘመናዊ አካሄድ ሐዲዱን የሚያስት ነው የሚሆነው።

እየሠሩ በመታደስ እየታደሱ በመሥራት መርሕ የሚረጋገጥ የሕግ የበላይነት፤ ዜጎች በምንም ዓይነት ሁኔታ ለጥቃት እንዳይጋለጡ፣ የሚወጡ ሕጎች በሙሉ መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩ፣ እነሱም በአግባቡ ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ ፍትሕ እንዲሰፍን እና የዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች እንዲከበሩ ይጠቅማል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚገነባውም ሆነ አገር ሠላም የምትሆነው እንዲህ ዓይነት ውስብስብ ሂደት ታልፎ በሚገነባ ሥር ያለው ሥርዓት እንጂ የአንድ ሰሞን በሚሆን ተሃድሶ አይደለም።

ባጠቃላይ፣ የመጨረሻው የሥልጣን ባለቤት ሕዝቡ በመሆኑ፤ በሕዝቡ ይሁንታ የጸደቁትን ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ተግባራዊ የማድረግ፣ ሠላምና መረጋጋት እንዲፈጠር፤ በጥቅሉ የሕግ የበላይነት የነገሰባት አዲስ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ዕውን በማድረግ ሂደት የፍትሕ አካላቱን ጨምሮ ሕዝቡም ስለሕግ የበላይነት ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚጠበቅበት መሆኑ ለድርድር መቅረብ የለበትምና እየሠሩ በመታደስ እየታደሱ በመሥራት ሂደት ውስጥ አሁንም ከሁላችንም ያልተቀዛቀዘ ተሳትፎው ይጠበቃል። አንዳንድ ንቅዘቶች ከጥልቅ ተሃድሶው በኋላም እየታዩ ነውና መንግሥታችን እየሠሩ መታደስን፤ እየታደሱ መሥራትን ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋው አይገባም።